# ፍትሕን ጥበቃ -- እስከ መቼ ?

በልጅግ አሊ

የትውልድ ትውስታዎች በሚል ርዕስ አንድ በመረጃ የተቀነባበረ(Documentary Film) ፊልም በዚህ ወር መጀመሪያ አካባቢ በካናዳ ዊኒፔግ ከተማ ለሕዝብ ቀርቧል። ይህ ፊልም በደርግ የአስተዳደር ዘመን በወጣቱ ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ጭፍጨፋ ቀይ ሽብርን ያስታውሳል።ፊልሙን ተሠርቶ ለሕዝብ እንዲቀርብ ያደረጉት አቶ አሊ ሁሴንን ናቸው።አቶ አሊ ራሳቸው የቀይ ሽብር ሰለባ በመሆን አዲስ አበባ በሚገኘው ከርቸሌ በመባል በሚታወቀው እስር ቤት ውስጥ ታስረው ነበር። አቶ አሊ ሁሴን ያንን የመከራ ጊዜ ለዛ ባለው ጨዋታቸው ያረሳሱን እንደነበር በወቅቱ አብረዋቸው ታስረው የነበሩ ሁሉ አይረሱትም። በደርግ ፅህፈት ቤት ውስጥ አሰቃቂ ግርፋት የደረሰባቸውን እስረኞች ወደ ከርቸሌ በተዘዋወሩ ጊዜ አቶ አሊ ሁሴን ያደርጉት የነበረው እርዳታም የሚዘነጋ አደለም።

ዛሬ **ያ ትውልድ** የተሰዋበት ዓላማን እያጣመሙ፣እያወላገዱ የሚያቀርቡ እጃቸውን በንፅሃን ደም የታጠቡ ብዙ ናቸው። ልጆቻቸው በቀይ ሽብር የተገደሉባቸው ወላጆች ፍትሕን ሳያገኙ ልባቸው እንደቆሰለ ፣ጧሪ አልባ ሆነው በሞት ከዚህ ዓለም እየተለዩ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ በነፍሰ ገዳይነት በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈው የነበሩት አብዮት ጠባቂዎች ፣ የደርግ አባላት ፣የኢሠፓ አባለት፣ የመኢሶን አባላት ወዘተ ደግሞ ዛሬ በውጭ አገር በተንደላቀቀ ኑሮ ውስጥ ይገኛሉ።አንዳንዶቹ እንዲያውም በተቃዋሚው ጎራ በሚገኙ በዘር ድርጅቶች ውስጥ ጋሻ ጃግሬ በመሆን ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ተዘጋጅተዋል። የቀይ ሽብሩ መሪ መንግሥቱ ኃይለማርያም ዙምቡዋቤ ውስጥ በተንደላቀቀ ኑሮ ውስጥ ይገኛል።

ምንም የደርግ መንግሥት ቢወድቅም በቀጣይነት የተተካው ሌላው ጨፍጫፊ የዘረኞች መንግሥት የሆነው ወያኔ በኢትዮጵያውያን ደም ከደርግ ያላነሰ ተጠያቂ ነው።ወያኔ ስልጣን በያዘ ሰሞን ደጋፊ ለማሰባሰብ ሲል የቀይ ሽብርን ጉዳይ ጀምሮ እንደነበር የሚታወስ ነው።ቀይ ሽብርን እንደ ማስፈራሪያ በመጠቀም ወያኔ ነፍሰ ገዳዮች እንዲያገለግሉት ማድረጉ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ወያኔ ሃገራችንን ለማጥፋት የሚያደርገውን ጥረት ለመቃወም ሲባል የቀይ ሽብርን ጉዳይ በተወሰነ ደረጃ ወደ ኋላ የተተወ ጉዳይ ነበር። ዘመኑ የተጋላቢጦሽ ነውና „የተወጋ ቢረሳ የወጋ አይረሳ“ እንዲሉ ገዳዮች በቀይ ሽብር በጣም የተጎዳውን ድርጅት ኢሕአፓን ከሕዝብ እንነጥላን ብለው አደባባይ መፎከር ጀምረዋል። እነዚህ የደርግ ጋሻ ጃግሬዎች በደርግ ጊዜ ኢሰብአዊ ድርጊትና ምዝበራን ሲፈጽሙ ሲያካሂዱ ከርመው ፣በሃገር ውስጥ ያለው ሁኔታ ሳይመቻቸው ደግሞ ሀገራችን ያላትን ንብረት ዘርፈው በየምዕራብ አገሮች ውስጥ በመሸሽግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጭቆና ነጻ እንዳይወጣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እየታገሉ ነው። ከወያኔ መንግሥት መውደቅ በኋላ ሥልጣን በእጃቸው ውስጥ እንዲገባ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።ፍትሕን የሚያስተካክል ሕዝባዊ መንግሥት ተቋቁሞ እነርሱ በሠሩት ግፍ እንዳይጠየቁ በከፍተኛ በመታገል ላይ ናቸው።

ቀይ ሽብርን በተመለከተ በኢትዮጵያና በካንቦዲያ የተፈፀሙ ድርጊቶች ተመሳሳይነት ያላቸው ይመስለኛል ።በሁለቱም ሃገሮች በሕዝብ ላይ የነበረውን ጭቆና እናስወግዳለን በማለት በኢትዮጵያ የደርግ መንግሥት በመንግሥቱ መሪነት ፣ በካንቦዲያ ደግሞ የካምር ሩዥ መንግሥት በፖልፖት መሪነት ወደ ሥልጣን ወጥተው ነበር።ሁለቱም መንግሥቶች ለሕዝብ የገቡትን ቃል በማጠፍ የነበረውን ብሩሕ ተሰፋ አጨልመውት አልፈዋል።ከዚያም አልፈው ተርፈው ሃገሮቹን እስርቤቶች ፣ ሕዝቡን በገዛ ሃገሩ ይህ ነው የማይባል ግፍ እንዲደርስበት አድርገውታል።ሁለቱም መንግሥቶች በዓለም ታሪክ ውስጥ የማይረሳ ስቃይን ፣ ጭፍጨፋን ፈፅመው አልፈዋል።

በካንቦዲያ በዚህ አሰቃቂ ዘመን የእስር ቤቱ አላፊ የነበረው <<ጓድ ዱኽ>> ( Comrade Duch) የተባለው ግለሰብ የሠራው ግፍ እንቅልፍ ስለነሳው ጥፋቱን አአምኖ ሕዝብን ይቅርታ እጠይቃለሁ ብሎ ተነሳስቷል የሚለው ዜና አለም አቀፍ የዜና ማሰራጫዎችን አጣቦ ከርሟል። ይህ ግለሰብ ለ 10000 ሰዎች

ሕይወት መጥፋት ተጠያቂ መሆኑንን አምኗል።የሚያሳዝነው ግን የእሱ ተባባሪ የነበሩት የዛን ወቅት ባለሥልጣናት አሁን ምንም ወንጀል እንዳልሠሩ እያካዱና <<የዱድ ዱኽ>> ይቅርታንና የፍርዱን ሂደት በማጣጣል ላይ ናቸው።

በካንቦዲያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት <<ዱድ ዱኽ>>በሦስት ወንጀሎች ተከሶ ፍኖን ፔን ከተማ ውስጥ ለፍርድ ቀርቧል። በሰው ዘር ላይ ወንጀል መፈፀም ፣ የሰው ዘርን ማሰቃየት፣ 10000 ግለሰቦችን ሕያወት ማጥፋትን ይመለከታል።እውነተኛ ስሙ ( Kaing Guek Eav) የሆነው <<ዱድ ዱኽ>> ከሌሎች አራት ባለስልጣኖች ጋር ነው ለፍርድ የቀረበው። ይህ አሁን 66 ዓመት የሆነው ግለሰብ ጥፋቱን ያመነና እራሱን ለፍርድ ያቀረበ ብቸኛ ግለሰብ ነው። ፕንኖን ፔን ውስጥ <<የዱድ ዱኽ>> ወንጀል በሚነበብበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በሃዘን ነበር የተሞላው። ይህ ግለሰብ አሠቃቂ የሆነ የማሠቃያ መንገድ ይጠቀም እንደነበር አምኗል። የተሰጠው ሃላፊነት በእሥር ቤት ውስጥ በማሰቃየት ምሥጢርን ማግኘት ነው። ምሥጢሩ ቢገኝም ባይገኝም እሱ በሚመራው እስር ቤት ውስጥ የሚገኙት እስረኞች መጨረሻቸው መረሸን ነው። ፈረንሳዊ የሆነው የተከሣሹ ጠበቃ ደንበኛው ያሰቃያቸውና የገደላቸውን ካንቦዲያውያን ቤተሰቦች በተገኙበት ይቅርታ መጠየቅ እንደሚፈልግ አሳስቧል። ይህንን ፍርድ የሚጠብቁ ብዙ እንደሆኑ የሚታወቅ ነው ። ምንም ቢቆይ ፍትሕ ለእነርሱ እየደረሰች ነው። እነዚህ ልጆቻቸውን ፣ ባሎቻቸውን ፣ ሚስቶቻቸውንን ፣ አባትና እናቶቻቸውን ያጡ ብዙ ዓመታት ይህንን ቀን ጠብቀውታል። ይህ ቀን እንዲደርስ የተባበሩት መንግስታት ጥረት አድርጓል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሃገሪቱ ዜጎች በግፍ ተጨፍጭፈዋል። በዚያ ወቅት ሃገሪቷ በሙሉ ወደ እስር ቤትነት ተለውጣ ነበር። አብዮት ጥበቃዎች፣ የደርግ አባላት ፣ የመኢሶን አባላት ወዘተ ጅምላ ጭፍጨፋ ለይ ነበሩ።የደም ጎርፍ አገሪቱን አጥለቅልቋት ነበር።ይህ ጊዜ በሃገራችን ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ታሪክ ውስጥ ለብዙ ዘመናት የሚታወስ ነው።በአሁኑ ወቅት ልጆቻቸው የተገደሉባቸው ወላጆች ፍትሕን ሳያገኙ በእድሜ ብዛት ከዚህ አለም ኑሮ እያለፉ ናቸው። እነዚህ አባትና እናቶች በየቀኑ እያለቀሱ ልጆቻቸውን እያስታወሱ ፍትህን ከሠላሳ ዓመታት በላይ ጠብቀዋል። ግን የሚያሳዝነው ጉዳይ በተሠራው ግፍ አንፃር ፍትሕን ለተበደሉት ፣ የተገፉት አባትና እናቶች ሊያገኙ አልቻሉም።

በካንቦዲያ ውስጥ የአሁኑ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስተር ሁን ዜን (**Hun Sen**) ከዚህ በላይ ወንጀለኞችን ወደ ፍርድ ማቅረብ ሃገራችንን እርስ በርስ ጦርነት የወስዳታል በማለት የተጀመረው የፍትሕ አሠራር እንዲቆም መከራከሪያ ነጥቡን አቅርቧል። የሰባአዊ መብት ድርጅት መሪዎች ግን ጠቅላይ ሚኒስተሩ በመንግሥቱ ውስጥ አሁን ሥልጣን ላይ የሚገኙ የካሜር ሩዥ ባለስልጣናት እንዳይጋለጡበት የሚያደርገው ጥረት ነው ብለው ተቃውመውታል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔን መንግሥት ለመጣል በሚደረገው ትግል የቀይ ሽብር ፍትሕ መጠየቅ ትግሉን ያዳክመዋል ብለው የሚያምኑ ትንሽ አይደሉም ። ይህ ቢሆንም ደግሞ በሌላ በኩል የቀይሽብር ተጠያቂዎች አሁንም ቢሆን በሠሩት ስራ ተፀፅተው ሕዝብን እንደ <<ዱድ ዱኽ>> ይቅርታ ሲጠይቁበት የታየ መድረክ የለም ። እንዲያውም አልፈው ተርፈው ጭፍጨፋው ትክክል ነው ብለው ለማሳመን እንካ ሰላምቲያ የጀመሩበት ወቅት ነው ። በሌላው በኩል የንፁሃንን ደም በማፍሰስ ከደርግ ያልተሻለው ወያኔ ፍትሕ ይሠጣል ብለን ለማመን ይከብደን ይሆናል። ነገር ግን እንደ ካንቦዲያ የተባበሩት መንግሥታት የሚያዘጋጀው ፍርድ ቤት ተዘጋጅቶ ፍትህን ለተበደሉት ለመስጠት ቢሞከር የሚከለክለው ምንም ምክንያት አይኖርም።እነ መንግሥቱ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች እንዲጠየቁ ትግል ቢደረግ ከወያኔ ጋር ያለውን ትግል ይበልጥ ያጠናክረዋል እንጂ አይጎዳውም ። ፍትሕ ይሰንብት እንጂ ለተበዳዩ መሰጠት ያለበት መሆኑን ነው ሁላችንም ማመን ያለብን። ከወያኔ ጋር የሚደረገውን ትግል እንዳይጠናከርና ወግ እንዳይኖረው የሚያደርገው ቀደም የተሠሩ ወንጀሎች እንዳይነሱ ስንከላከል ነው። ይህ አልፎ ተርፎ በወያኔ መንግሥት ውስጥ ሆነው የንጹሃንን ደም ያፈሰሱ ሳይቀሩ ይቅርታ ይደረግላቸው የሚሉ አሉ። ማን ነው ይቅርታ አድራጊው? ምንስ ወንጀል ነው ይቅርታ የሚደረግለት? እንዴትስ ነው ይህ ይቅርታ የሚደረገው? እነዚህ ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው።

ለፍትሕ መቆም የሰው ዘር ሁሉ ሃላፊነት ነው ብዬ ባምንም በወቅቱ የኢሕአፓ አባላት የነበሩ እጥፍ ድርብ ሃላፊነት አለባቸው። ምክንያቱም አብረው ለአንድ ዓላማ ሲታገሉ የነበሩ ጓዶቻቸው በትግሉ ተሰውተዋልና ነው። ግን ይህ ሃላፊነት የማይሰማቸው ጥቂት አይደሉም። በዚያ ወቅት የተሰዉ ወጣቶች

ለሃገራችን እድገት በንጹህ ልቦና መሰዋታቸውን ከቀድሞ ጓዶቻቸው ሌላ ማን ሊመሰክር ይችላል? በግፍስ በአሰቃቂ ሁኔታ እንደተሰቃዩ ማን ለዓለም ማስረዳት ይጠበቅበታል? ሂዱ እንከተላችኋለን ብለናቸው ቀድመው የተሰዉትን ወጣቶች ሲንቋሸሹ የሁላችንም ውርደት ሊሆን ይገባል።እነዚህ ወጣቶች ዛሬ እበላ ባይ ዶክተርና ፕሮፌሰር ከመንግሥት መንግሥት እየተራወጠ የራሱን ክብር የሚገነባ እዩኝ ባይ ሊያዋርዳቸው አይገባም። ዛሬ ገና እስር ቤት ሲያስገቡት እግር ላይ ወድቆ ይቅርታን የሚለምን መሰዋትነት ምን ያህል ከባድ መሆኑን ሊረዳው በተገባ ነበር። የገዳዮች የፖለቲካ መሪ ባለስልጣን የነበረ ዳግም ቀይ ሽብር እንዲያኪያሂድ ወደ ሥልጣን እንዲመጣ ሊፈቀድለት አይገባም።

ለመገደል ታስረው ሲወሰዱ ይቅርታ ጠይቀው በባንዶች እግር ላይ ወድቀው አልቅሰው ሕይወታቸው ማትረፍ እንደ አሁኖቹ ዘመናይ ፖለቲከኞች አጥተውበት አልነበረም። የእነርሱ ለቆሙለት ዓላማ መሰዋት ሃገራችን ዛሬ ከደረሰችበት የውርደት አዘቅት ውስጥ እንዳትገባ ቀድሞ በማሰብ ነበር። በዘር ሳይለያዩ በአንድነት ወደ መቃብር የወረዱትን ወጣቶች ከወያኔ ጋር ሆኖ "የአማራ ሕዝብ ከየት ወዴት " ብሎ የፃፈ የወያኔ ካድሬ የደርግ ነፍሰ ገዳዩችን ሰብሰቦ ሲሰድባቸው እንደሚውል የሚታወቅ ነው። ትላንት በገዳዮች ጎራ ቆሞ በደርግ " የፍየል ወጠጤ " ማርሽ ሲደንስ የነበረ የመኢሶን አባል ዛሬ አጥንታቸው ላይ በመቆም ወደ ሥልጣን ኮርቻ ለመፈናጠጥ ሊፈቀድለት አይገባም።

ፍትሕን ለሚጠብቁ ፍትሕ እንዳይደርስ ማድረግ እራሱን የቻለ ወንጀለኝነት ነው። ፍትሕ አንድ ቦታ ጎደለ ማለት ሁሉም ቦታ ፍትሕ ጎደለ ማለት ነውና ሁላችንም ለፍትሕ መጠበቅ እንታገል።ለሃገራቸው የተሰዉትን ወጣቶች የምንታደጋቸው ፍትሕን በማምጣት ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የኢሕአፓ አባል መሆን ፣ በኢሕአፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ማመን ወይም በቀይ ሽብር የተገደለ ዘመድ እንዲኖረን አያስፈልግም። የሚጠይቀው ለሰብአዊ መብት መቆምን ነው። የሚጠይቀው ለእውነት መቆምን ነው።

አቶ አሊን እንደ ምሳሌ በማድረግ ሁላችንም የምንችለውን ማድረግ ይኖርብናል።በዚሁ አጋጣሚ አቶ አሊ ሁሴንን ይህንን አረመኔያዊ ተግባር ለማጋለጥ ያደረጉትን ጥረት ከልብ አመሰግናለሁ።

ሰለተሰዉት የሚያስብ በሰላም ይክረም !!!!!